# QUICKNOTES mcps

**ጃኑዋሪ 9/2019 QuickNotes**

## ስለ ውጤት/ማርክ አሰጣጥ እና ምዘና/ፈተና ከሚስተር ስሚዝ የትምህርት ቤቶች ዋና የበላይ ተቆጣጣሪ/Superintendent Smith የተላለፈ መልእክት፡-

ምናልባት ካመለጠዎት፣ ከትምህርት ቤቶች ዋና የበላይ ተቆጣጣሪ ጃክ ስሚዝ/Superintendent Jack Smith ስለ ማርክ አሰጣጥ እና ሪፖርት አቀራረብ የተላለፈውን መልእክት ማግኘትዎን ያረጋግጡ።

ውድ ወላጆች እና አሳዳጊዎች፡-

ምናልባት እርስዎም አንብበው ወይም ሰምተው ይሆናል፡- የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የማርክ አሰጣጥ እና የምዘና ፖሊሲ ባለፉት በርካታ ሣምንታት በሚዲያ የመነጋገሪያና የውይይት ርእስ ሁኖ ነበር። ስለ ውጤት እና ሪፖርት አሰጣጥ በመደበኛነት እንደምንወያይበት ሁሉ፣ ባለፈው ዲሴምበር 4/2018 በትምህርት ቦርድ ስብሰባ ላይ የተደረገውን ጠንካራ ውይይት ጨምሮ፣ በትምህርት ቤታችን ሥርዓት ውስጥ ስለ ውጤት አሰጣጥ እና ግምገማ አንዳንድ የቁልፍ ነጥቦችን አውድ ለእርስዎ በቀጥታ ለመግለጽ እፈልጋለሁ።

የክፍል ውጤት አሰጣጥ ዓላማው ተማሪዎች ምን እንደሚያውቁ እና ምን እንደተማሩ በማንፀባረቅ እንዲያገለግል ነው። ነገር ግን ስለ ተማሪ የመማር ሁኔታ ማርክ መስጠት ከበርካታ መመዘኛዎች/መለኪያዎች አንዱ ብቻ ሆኖ መታየት ይኖርበታል። ለምሣሌ፡- ACT፣ SAT፣ AP/IB፣ ከዲስትሪክት የሚሰጡ ምዘናዎች፣ የሙያ ሠርተፊኬቶች፣ እና የስቴት ምዘናዎች፣ እያንዳንዳቸው "ስለተማሪ አሠራር እና ችሎታ የተለያየ ገፅታ ስለሚለኩ ጠቃሚ መረጃዎችን ይሰጣሉ።" በእኛ የመማር ማረጋገጫ ማዕቀፍ፣ የሁሉንም ተማሪዎች እርምጃ ለመለካት በጋራ እነዚህን መመዘኛዎች እንጠቀማለን።

በጠቅላላ በአገሪቱ፣ የትምህርት ሥርአቶች በየትምህርት ቤቶቻቸው፣ በእያንዳንዱ መማሪያ ክፍል፣ ለእያንዳንዱ ተማሪ ይህ እንደሚሠራ ለማረጋገጥ ጥረት ላይ ናቸው። ይህንን የጋራ ዓላማ በመፍጠር እና በማካፈል ረገድ MCPS የመሪነት ሚና አለው።

ጁላይ 2016 እኔ ከመምጣቴ በፊት ባለፉት ሁለት አሥርተ ዓመታት በ MCPS ልጆች የነበራችሁ፣ ስለ ውጤት/ማርክ አሰጣጥ እና ሪፖርት ፖሊሲዎች እና ፕሮቶኮሎች በአብዛኛው የተቀየሩት በነዚያ ወቅቶች እንደነበረ ታውቁ ይሆናል። በዚህ ማስታወሻ እንደተጠቀሱት ዋና ሃሳቦች፣ ከ 2000 ጀምሮ ማርክ/ውጤት አሰጣጥ ላይ ተጽዕኖ ያደረጉ ተከታታይ ለውጦች ተደርገዋል፣ Algebra 1 ዲስትሪክት አቀፍ የማጠቃለያ ፈተና አስተዳደርን ጨምሮ፤ የሜሪላንድ የኮሌጅ እና የስራ ዝግጁነት ሥነ-ሥርአት/መደበኛ አሰራር በሥራ ላይ ማዋል/መቀበል፤ከእርምጃ ምዘናዎች/ማጣሪያዎች ጋር-የተጣጣመ፣ ወደ በለጠ ተደጋጋሚ መመዘኛ ሽግግሮች፤ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ውጤትን ለመተካት የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኮርስ በድጋሚ እንዲወስዱ

መፍቀድ (Drop and Replace)፤ እና የሁለተኛ ደረጃ ኮርሶች የስሜስተር ዉጤት/ደረጃ ስሌት በመከለስ የማቆልቆል አዝማሚያ ስሌትን ለማስወገድ እና በሂሳብ የውጤት ስሌት የመተካት።

የ 2018 ክፍሎች የቅርብ ጊዜ መረጃ እንደሚያመለክተው በውጤታቸው ለተማሪዎች የተሰጣቸዉ የAዎች ቁጥር ጨምሯል። ይህ መጨመር በትምህርት ቤቶቻችን የማርክ አሰጣጥ ግሽበት እየተካሄደ ይሆናል በማለት አንዳንድ ሰዎች ስጋታቸዉን እንዲገልጹ አድርጓቸዋል። በተለይም ሁለት ለውጦች (transition to progress checks and Drop and Replace) ተግባራዊ የተደረጉት በሁለተኛ ደረጃ እያሉ ስለነበረ፣ በ 2018 ክፍሎች ላይ ተፅእኖ ማድረጋቸውን መገንዘብ አስፈላጊ ነው።

ስለ ውጤት ግሽበት ስጋቶችን አጽንኦት ሰጥተን እንመለከታለን። የማርክ/ውጤት ግሽበት በሚከሰትበት ጊዜ፣ ለአንዳንድ ተማሪዎች ውጤታማ መሆናቸውን የውሸት ስሜት እና በሌሎቹ ላይ ደግሞ የውሸት ውድቀት ስሜት ይፈጥርባቸዋል።

ከ 2016 ጀምሮ፣ የምዘና እና ውጤት አሠጣጥ ተግባሮችን ውጤቶች ተማሪ መማሩ(ሯ)ን በትክክል የሚያንፀባርቁ መሆናቸውን ከሌሎች መለኪያዎች ጋር በማነፃፀር በተከታታይ እየተከታተልን ነው። ግኝቶቻችን ላይ ተመስርተን የማስተካከያ አስተያየቶችን እያቀረብን ሲሆን በቀጣይ ለማቅረብም ዝግጁዎች ነን።

በቅርቡ MCPS ተማሪዎች ውጤት በሚመዘገብላቸው ኮርሶች ላይ መመደብ ይኖርባቸው እንደሆነ ለመወሰን ACCUPLACER (college entrance/placement exam to determine whether students should be placed in credit-bearing courses) የተመረጡ የ MCPS ኮርሶች ውጤት በተማሪዎች ላይ ያለውን ተጽእኖ ለመዳሰስ ከሞንትጎመሪ ኮሌጅ (Montgomery College) ጋር ትብብር እያደረገ ነው። ለእነዚህ ተማሪዎች በመምህራኖቻቸው አማካይነት የሚሰጣቸው ውጤት በክሬዲት ለሚወሰዷቸው ኮርሶች ውጤታማ እንደሚሆኑ የተሻለ አመላካች ነው። ACCUPLACER፣ በአንድ ብቻ ቴስት/የፈተና ውጤት እነዚህኑ ተመሣሣይ ተማሪዎች እንደ አንድ ብቸኛ ቴስት/ፈተና/መመዘኛ፣ በ "remedial class" ሊያስቀምጣቸው ይችላል።

በውጤት አሰጣጣችን እና የምዘና ልምምዶቻችን ላይ የተደረጉት ለውጦች እኛ እንዳሰብነው የተማሪን መማር የሚያንፀባርቁ ሆነው ያለመገኘት ያልታሰበ አቅጣጫ አምርተው ሊሆን ይችላል። በሌላ በኩል ደግሞ ቀድሞ ይሠራበት የነበረው የማጠቃለያ ፈተናዎች እና ዝቅተኛ የውጤት አሰጣጥ ስሌት የተማሪን ውጤታማነት ይጫን እንደነበረና የአሁኑ ውጤት አሰጣጥ የተማሪን የመማር ሁኔታ በተሻለ መልኩ የሚያንፀባርቅ ይሆናል። የ 2013 መረጃ የማጠቃለያ ፈተና ሞዴል በተማሪዎች ውጤታማነት ላይ እንዴት ተጽእኖ እንደሚያደርግ እና እንደማያደርግ ያሳያል። በዚህ መረጃ መሠረት፣ ወደ ቀድሞው አይነት ሞዴል/አሠራር መመለስ ስህተት ይሆናል። መምህራን ለተማሪዎቻቸው የትምህርት አቀባበል የሚጠቅም ሆኖ ካገኙት ማጠቃለያ የክፍል ፈተና ለመስጠት የሚያግዳቸው ነገር እንደሌለ መታወቅ አለበት። ይልቁንም፣ ከፖሊሲ ጋር የማይገናኙ፣ለተማሪዎች ማሻሻል መሠረት የጣሉ የተሻሻለ የመምህር ትግበራ እና  ለትክክለኛ የተማሪ መረጃ የበለጠ ተደራሽነትን የሚያካትቱ ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ። ቀጣይ ትንታኔያችን ማናቸውም እነዚህ ሊሆኑ የሚችሉ ሁነቶች በማረጋገጫ/ማስረጃ የሚደገፉ እንደሆነ ለመወሰን ይረዳናል።

በመላ አገሪቱ በሚካሄዱት የትምህርት ሥርዓቶች በደርዘን የሚቆጠሩ የማርክ/ውጤት አሰጣጥ ሥርአቶች ያሉ ሲሆን የትኛውም ፍጹም አለመሆኑን ጥናቶች ያመለክታሉ። የምናውቀው ነገር፣ ማርክ/ውጤት አሰጣጥ የተማሪን ትምህርት ከሁሉም በላቀ ለመገምገም ማስቻል ላይ ማዕከል ማድረግ እንዳለበት ነዉ። ፖሊሲዎቻችን እና አሠራሮቻችን ይህንን ግባችንን ለማንፀባረቅ የሚኖራቸውን ተፅእኖ መከታተልን MCPS ይቀጥላል።

ከማክበር ሰላምታ ጋር

ጃክ አር. ስሚዝ (ዶ/ር) Jack R. Smith, Ph.D.
የት/ቤቶች ዋና ተቆጣጣሪ Superintendent of Schools

**የአእምሮ ጤንነት እና የጤናማነት አቋም ውይይት-መድረክ ጃኑዋሪ 12 ይካሄዳል**

2ኛው ዓመታዊ የአእምሮ ጤንነት እና የጤናማነት አቋም ውይይት-መድረክ ቅዳሜ ጃኑዋሪ 12 ከ 1–5 p.m. በ ኢርል ቢ. ውድ መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት/Earle B. Wood Middle School ይካሄዳል።

በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ/MCPS እና በሞንትጎመሪ ካውንቲ PTAs ካውንስል (MCCPTA)፣ ትብብር የሚካሄደው ይህ ዝግጅት ዛሬ ወጣቶች ስለሚያጋጥማቸው የአእምሮ ጤንነት ተግዳሮት ላይ መወያየት እና በ MCPS እና በአጠቃላይ ማህበረሰቡ ዉስጥ ያሉት መርጃዎች/ሪሶርሶች ይቀርባሉ።

በአሥራዎቹ እድሜ ክልል የሚገኙ ወጣቶች ላይ ድብርት/መጨፍገግ፤ ውጥረትና ጭንቀት/ ከስጋት፤ ሱስ ከሚያስይዝ አደንዛዥ እፅ/ኦፒዮድስ፤ የ LGBTQ ተሞክሮዎች፤ ራስን መጉዳት እና ራስን ማረጋጋት ባህርዮች፤ BTheOne Campaign for Peer Support፤ የመተማመንን ባህል ስለመገንባት፦ከኖርዝውድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት/Northwood High School፤ እና በብዝሃነት ባህል ውስጥ ከፉኛ የተጎዳ ስሜትን ስለማከም በተከፋፈሉ ክፍለጊዜያት ትምህርት ይሰጣል።

ልዩ ገፅታዎቹ የሚያካትቱት በገላጣ ቦታ ላይ መሠወር/መደበቅ (የወላጆችን ፈልጎ የማግኘትን ክህሎት ለማጠናከር የተነደፈ፤ ለጎልማሳ ሰዎች ብቻ)፤ የናርካን ስልጠና/Narcan training (ለጎልማሶች ብቻ)፤ነፃ የአእምሮ ጤንነት የመጀመሪያ እርዳታ ስልጠና ከ 8:30 a.m.–5 p.m ይሰጣል፤ እና የሪሶርስ ጠረጴዛዎች። ከ 4–5 p.m. በ አናንያ ታዲኮንዳ/Ananya Tadikonda የትምህርት ቦርድ አባል የሚመራ የተማሪ ምላሽ ውይይት ክፍለጊዜ ይካሄዳል።

ውድ መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Wood Middle School) የሚገኝበት አድራሻ፦ 14615 Bauer Dr. in Rockville ነው።

ተጨማሪ መረጃ

እዚህ ይመዝገቡ።

**የወላጅ አካደሚ አውደጥናቶች/Parent Academy Workshops ለወላጆች ጠቃሚ መገልገያ መሣሪያዎችን ይሰጣሉ**

የ MCPS የወላጅ አካዴሚ ለወላጆችና ለማህበረሰብ አባላት የልጆቻቸውን የት/ቤት ስኬት የሚያግዙ መረጃዎች፣ መገልገያዎች፣ መሳርያዎችና ምክሮች የሚሰጡ ዎርክሾፖች ለመከታተል እድል ይሰጣሉ።

የ 2019 የክረምት ወራት ዎርክሾፖች ጀምሯል። ስለ ጥንቃቄ፣ የኮሌጅ እና ሥራ ዝግጁነት እቅድ/ፕላን፣ስለ ESOL መርጃ መሣሪዎች እና ሌሎችም በርካታ ጉዳዮችን ውይይት የሚደረጉባቸውን ክፍለጊዜያት እንዲያመልጥዎት አይፈልጉም።

የወላጅ ኣካዴሚ ዎርክሾፖች ነፃ ናቸው። የልጆች እንክብካቤና የትርጉም ኣገልግሎቶች በሁሉም ስብሰባዎች/ክፍለጊዜዎች ይቀርባሉ። በወላጅ አካደሚ አውደጥናት ድረ-ገጽ/Parent Academy website ላይ ጠቅላላ የኮርሶቹ ዝርዝር ይገኛል፦ https://www.montgomeryschoolsmd.org/departments/parentacademy/። እዚህ ለመመዝገብ ይችላሉ፦ https://stultzde.wufoo.com/forms/winter-2019-parent-academy-workshop-registration/። በአጭሩ የተጻፈ መግለጫ ከዚህ በታች ይገኛል።

**በህዝባዊ ትምህርት ልዩ የሆነ አስተዋጽኦ ላበረከቱ ዓመታዊ ሽልማት ለመስጠት ተጠቋሚዎች/እጩዎች ይፈለጋሉ**

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ለ22ኛው ዓመታዊ ሽልማት በህዝባዊ ትምህርት ታዋቂ አገልግሎት ያበረከቱ ሰዎችን ጥቆማ ማግኘት ይፈልጋል። ሽልማቶቹ ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ህዝባዊ ትምህርት በምሳሌነት የሚጠቀስ አስተዋጽኦ ያበረከቱ ለግለሰቦች፣ (ተማሪዎችን ጭምር)፣ ቡድኖች እና ድርጅቶችን እውቅና ለመስጠት እና አድናቆት ለመግለጽ በቦርድ አማካይነት የተዘጋጀ/ስፖንሰር የተደረገ ነው።

ጥቆማዎች በሚከተሉት ዘርፎች ተቀባይነት ይኖራቸዋል፡-

- የማህበረሰብ ግለሰብ (ተማሪዎችንም ማካተት የሚችል)
- የማህበረሰብ ቡድን
- ቢዝነስ/ንግድ
- MCPS ሠራተኞች
- የትምህርት ቤት አገልግሎት በጎ ፈቃደኛ
- አዲስ ነገር በማመንጨት ታዋቂ የሆነ/ች ግለሰብ

"የታዋቂ ግለሰብ ሽልማት" በአሁን ወቅት ምናልባት በሥራ ላይ የማይገኙ ቢሆኑም፣ ከዚህ በፊት ልዩ እና ከፍተኛ አስተዋጽኦዎችን ያደረጉ ተጠቋሚዎች ናቸው። የተጠቋሚዎቹ አስተዋጽኦ ለረዥም ጊዜ በትምህርት ሥርዓቱ ላይ አዎንታዊ ተጽኖ ያሳደረ መሆን አለበት።

በሌሎቹ ዘርፎች የሚደረጉ ጥቆማዎች ባለፉት ሦስት ዓመታት ለህዝባዊ የትምህርት ሥርዓት በቁርጠኝነት ያገለገሉ እና የሚደግፉ ግለሰቦችን (የ MCPS ተማሪዎችን ጨምሮ)፣ ቡድን፣ ወይም ድርጅቶች እንደሚከተለው የሚገለጽ፡-

- ለትምህርት ሥርአት ፕሮግራሞች እጅግ ከፍተኛ የሆነ የጊዜ እና የእውቀት ጥበብ ያበረከቱ፣
- በተምሣሌትነት የሚገለጽ ፕሮግራም ወይም ፕሮጀክት ማጎልበት እና/ወይም ተግባራዊ ማድረግ፣ ወይም
- ሥርአት አቀፍ ጠቀሜታ የሚሰጥ ውጤት ያለው አስተዋጽኦ።

የጥቆማ ማቅረቢያ ቅጾች በ የትምህርት ቦርድ ድረ-ገጽ/Board of Education website ወይም ከቦርድ ጽ/ቤት ይገኛሉ። **የተሞሉ የጥቆማ ቅጾች ወደ ትምህርት ቦርድ ጽ/ቤት ማርች 1/2019 ከ 5 p.m. በፊት መድረስ አለበት።**

የተሞሉ ቅጾችንበፖስታ ይላኩ ለ ፡-
Montgomery County Board of Education
የካርቨር የትምህርት አገልግሎት ማእከል Carver Educational Services Center
850 Hungerford Drive, Room 123
Rockville, Maryland 20850
ፋክስ፡- 301-279-3860
ኢ-ሜይል

የበለጠ መረጃ ለማግኘት በሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ጽ/ቤት (Montgomery County Board of Education office)፡- Danielle Susskind ወይም Becky Gibson ን በስልክ ቁጥር፡- 240-740-3030 ማነጋገር ይችላሉ።

## ለአንደኛ ደረጃ እና ለሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች "Don't Be Distracted" የተሰኘ ውድድር ተከፍቷል

ከሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ውስጥ ከ4 ተማሪዎች ውስጥ 1 እና በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ውስጥ ከ6 ተማሪዎች 1 በተዘናጋ ሃሳብ እንደሚራመዱ ስለ ልጆች ደህንነት የተደረገ ጥናት ያመለክታል። እነዚህ መዘናጋቶች አብዛኛውን ጊዜ ቴክስት በመለዋወጥ ወይም በስልክ የጆሮ ማዳመጫ በማድረግ ነው። ለወጣት ልጆች አሽከርካሪዎች፣ ለሁለት ሰኮንድ ወይም የበለጠ ከመንገድ ውጭ በጨረፍታ ማየት የመጋጨት ወይም ለግጭት

የመቃረብ አደጋዎችን በአራት እጥፍ ይጨምራል። ተዘናግተው የሚያሽከረክሩ ወይም የሚራመዱ ተማሪዎች ራሳቸውን እና ሌሎችን በአደጋ ላይ ይጥላሉ። የሞንትጎመሪ ካውንቲ የመጓጓዣ ዲፓርትመንት ሁሉም የ MCPS ተማሪዎች በ 2019 በ "Don't Be Distracted Contest" ውድድር ላይ በመሳተፍ በዚህ ወሳኝ ጉዳይ ላይ ግንዛቤ በማስረፅ እንዲረዱ ይጋብዛል።

ተማሪዎች ከ30-60 ሰኮንዶች የህብረተሰብ ተሳትፎን የሚጋብዝ የማስታወቂያ (PSA) ቪድዮ ወይም የስነጥበብ ሥራ በሚከተሉት ርእሶች ላይ እንዲያዘጋጁ ይጠየቃሉ፦

1. ሳይዘናጉ ማሽከርከር ወይም መራመድ አስፈላጊነቱን/ጠቀሜታዉን ለጓደኞችህ(ሽ) ተናገር (ሪ)።
2. በተለይም በትምህርት ቤቶች አካባቢዎች ሳይዘናጉ ማሽከርከር በጣም አስፈላጊ መሆኑን ለአዋቂዎች/ለጎልማሶች ንገሩ(ሪያ)ቸው።

የመዘናጋቶች ምሳሌ፦

- ቴክስት እያደረጉ ማሽከርከር
- ቴክስት እያደረጉ መራመድ
- ስልክ እያወሩ እና እጅን ነፃ የሚያደርግ መገልገያ መሳሪያ ያለመጠቀም
- እየበሉ ማሽከርከር
- እየተቆነጃጁ ወይም እየተላጩ ማሽከርከር
- የጆሮ ማዳመጫ ሰክቶ መራመድ

ሁሉም ግብአቶች ሰኞ ማርች 4 መቅረብ አለባቸው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት እና ግብአቶችን ለማቅረብ ይህንን ድረ-ገጽ ይጎብኙ፦ https://www.montgomerycountymd.gov/DOT-PedSafety/SRTS/creative-contest.html።

**የ HBCU ዝግጅት/በዓል ፌብሯሪ 22 ይካሄዳል**

11ኛው ዓመታዊ የጥቁር ኮሌጆች እና ዩንቨርስቲዎች/Historically Black Colleges and Universities (HBCU) አውደ ርእይ ዓርብ ፌብሯሪ 22 ከ 6-8 p.m. በ Universities at Shady Grove, Building 3, 9640 Gudelsky Drive in Rockville ይካሄዳል። ከ4–8 p.m. በቦታው ላይ የመግቢያ/የመቀበያ ቃለመጠይቅ ይደረጋል።

ይህ በነፃ የሚካሄድ ዝግጅት ከ 8ኛ–12ኛ ክፍል ለሚማሩ ተማሪዎች ከ 60 በላይ በታሪክ የጥቁሮች ኮሌጆች እና ዩንቨርሲቲዎች/HBCUs ተወካዮችን ለማግኘት እድል ይሰጣል። የ HBCU ተወካዮች ብዙ መረጃ/ኢንፎርሜሽን ያቀርባሉ እናም ለተማሪዎች እና ወላጆች ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ። ዝግጅቱ ለመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች እና ለወላጆች ስለኮሌጅ ቅድመ-ዝግጅት አውደጥናት/ዎርክሾፕ፣ FAFSA ለመሙላት ዎርክሾፕ፣ ስለስኮላርሽፕ መረጃዎችን/ኢንፎርሜሽን እና በሌሎችም ያተኩራሉ።

በርካታ የ HBCU ተወካዮች ከ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ጋር በሥፍራው ቃለመጠይቅ ያደርጋሉ። ቃለመጠይቅ/ኢንተርቪው በሚደረግበት ወቅት ተማሪዎች የማመልከቻ/አፕሊኬሽን ክፍያ ሊሰረዝላቸው ይችላል፣ ስኮላርሽፕ የማግኘት እና እዚያው ምደባ የማግኘት እድል ይኖራል።

በድረ-ገጽ ላይ መመዝገብ ያስፈልጋል። እባክዎ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤትዎን የኮሌጅ እና ሥራ ኢንፎርሜሽን አስተባባሪ ወይም ካውንስለር ስለ ምዝገባው ያነጋግሩ።

[የ HBCU በአል]

**የኮሌጅ ፌር ላይ ጊዜአችሁን በውጤታማነት መጠቀም**

ከዝግጅቱ በፊት

- መፈተሻዎን እርግጠኛ ይሁኑ [አውደ ርእይ ድረ-ገጽ/fair website] እና የትምህርት ቤትዎን ካውንስለር ወይም የኮሌጅ እና የሥራ ኢንፎርሜሽን አስተባባሪ ስለ ምዝገባ ያማክሩ።
- የተሳታፊዎችን ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች ዝርዝር ተመልከቱና መጀመሪያ የትኞቹ ጋር መሄድ እንደምትፈልጉ እና በቂ ጊዜ ካለችሁ መጎብኘት የምትፈልጓቸውን በቅድሚያ ወስኑ።
- ለመዝጋቢ ሠራተኞቹ የሚያቀርቡትን ጥያቄዎች ዝርዝር ያዘጋጁ።

በዝግጅቱ/በትርኢቱ ወቅት

- በአግባቡ ይልበሱ።
- ካርታ ይኑራችሁ፣ ከፍሉን ቃኙ እና ለጉዞኣችሁ የአቅጣጫ ዕቅድ አዘጋጁ። ከከፍተኛ ምርጫዎቻችሁ ውስጥ ቢያንስ የ10ቹን ጠረጴዛዎች ለመጎብኘት ይሞክሩ።
- በሚፈልጉት የኮሌጆች የፖስታ መቀበያ ዝርዝሮች ውስጥ እንድትገኙ ተመዝገቡ።
- ከምትፈልጓቸው ኮሌጆችና ዩኒቨርስቲዎች መፅሄቶችን አንሱና እንድታነቧቸው ወደቤት ውሰዱ።
- በውይይት ወቅትና የኮሌጅ ተወካዮችን ስታገኙ ማስታወሻ ያዙ።

ዝግጅቱን ስፖንሰር የሚደርጉት MCPS፣ the Montgomery County Branch of the NAACP እና the Washington Inter Alumni council of the UNCF ናቸው።

**የዶ/ር ኪንግን ህይወት (Dr. King's Life) ለእርስዎ ማህበረሰብ አገልግሎት በመስጠት ያክብሩ**

ሰኞ ጃኑዋሪ 21፣ ዶ/ር ማሪቲን ሉተር ኪንግ ጁንየር /Dr. Martin Luther King Jr.ን ለማክበር በሺዎች የሚቆጠሩ ሌሎች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ተማሪዎች እና ቤተሰቦችን ይቀላቀሉ። በሞንትጎመሪ ካውንቲ የበጎፈቃድ አገልግሎት ማእከል/Montgomery County Volunteer Center's 2019 MLK የአገልግሎት ቀን በ Bethesda North Marriott and Conference Center, 1-3 pm. ህይወት እና አስተምህሮቶች በመሣተፍ።

ተሳታፊዎች ለሁሉም የዕድሜ ክልል ተስማሚ የሆኑ በርካታ በሆኑ የአገልግሎት ፕሮጀክቶች ላይ የመሣተፍ እድል ይኖራቸዋል፣ እና ተማሪዎች የተማሪ አገልግሎት ትምህርት (SSL) ሠዓቶችን ያገኛሉ። የሥራ እንቅስቃሴዎቹ ለረሃብተኞች ምግብ ከማሸግ አንስቶ እና ለእንስሳት መጠለያዎች አሻንጉሊቶችን/dog toys መስራት፣ ለደከሙ ህመምተኞች የአንገት ልብሶችን ማዘጋጀት እና ለጦር ኃይል ወታደሮች የአድናቆት ካርዶችን ማዘጋጀት የመሣሠሉ በርካታ ነገሮችን ያካትታል። በተጨማሪ:- አውደ ርእዩ ዓመቱን በሙሉ አብሮ የማገልገል እድል የሚሰጡ የተለያዩ የመንግስት ኤጀንሲዎችን እና የመንግስት ያልሆኑ ድርጅቶችን የመተዋወቅ እድል ይሰጣል።

ይህ ዝግጅት የሚካሄደው በነፃ ሲሆን፣ ነገር ግን ያለው ቦታ ውሱን በመሆኑ በቅድሚያ መመዝገብ ስለሚያስፈልግ [እዚህ ቦታ ይመዝገቡ]።

በተጨማሪ፣ Olney, Rockville, Silver Spring, Gaithersburg, እና Germantown የበርካታ መለስተኛ-ደረጃ ፕሮጀክት አገልግሎቶች በእለቱ ይሰጣሉ። [የማርቲን ሉተር ኪንግ ቀን የበጎፈቃደኝነት አገልግሎት ድረ-ገጽ/Volunteer Center's MLK Day web page] ለዝርዝር መረጃ እና ለመመዝገብ ይጎብኙ።

**በመጪዎቹ የካውንቲው የትምህርት በጀት ስብሰባዎች ላይ ያለዎትን ሃሳብ ያካፍሉ**

ወላጆች እና የማህበረሰብ አባላት የሞንትጎመሪ ካውንቲ ካውንስል አባል Craig Rice፣ Superintendent of Schools Jack R. Smith፣ እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ኮሌጅ ፕሬዚደንት/Montgomery College President DeRionne Pollard በመጪው ፌብሯሪ እና ማርች ላይ በሚካሄዱት የትምህርት ባጀት ስብሰባዎች ላይ ለመገናኘት ተጋብዘዋል። ተከታታዮች የበጀት ውሳኔዎች እንዴት እንደሚወሰዱ፣ ለFY 2020 እና ከዚያ ባሻገር ዝግጅት ካዊንቲው ምን ማድረግ ላይ እንደሚገኝ፣ እና በበጀት ውሳኔዎች ላይ ተፅእኖ ለማድረግ ነዋሪዎች ያሏቸው እድሎችን ማወቅ ይችላሉ።

ስብሰባዎቹ በሚከተሉት ቦታዎች ከ6:30 እስከ 8:30 p.m ይካሄዳሉ፡-

**ፌብሯሪ 20**፣ኒልስቪል መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት/Neelsville Middle School, 11700 Neelsville Church Road in Germantown

**ፌብሯሪ 27**፣ኮ/ል ብሩክ ሊ. መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት/Col E. Brooke Lee Middle School, 11800 Monticello Avenue in Silver Spring

**ማርች 6** ሮክቪል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት/Rockville High School, 2100 Baltimore Road in Rockville

**ማርች 11**፣ ቤተዝዳ-ቼቢ ቼዝ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት/Bethesda-Chevy Chase High School, 4301 East-West Highway in Bethesda

**ማርች 27** ፣ የሞንትጎመሪ ኮሌጅ ታኮማ ፓርክ ካምፓስ የባህል ቲያትር ማዕከል/Montgomery College Takoma Park Campus (Cultural Arts Center Theater 1)

ማርች ላይ የካውንቲው ዋና ኃላፊ ለ2019 የተያዘውን የበጀት እቅድ ያሳውቃል። በኤፕረል ወር፣ የካውንቲ ምክር ቤት ሸንጎ ያካሂድና የስራ ማስኬጃ በጀቱን በሜይ ወር መጨረሻ ያፀድቃል።